የሽግግር ፍትህ
TRANSITIONAL JUSTICE

## ጋዜጣዊ መግለጫ

ነሐሴ 13 2016 ዓ.ም

# የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የሽግግር ፍትሕ ትግበራ ፍኖተ-ካርታ ዝግጅት መጠናቀቅና የሕግ ማዕቀፎች ዝግጅት ሂደትን አስመልክቶ የተሰጠ መግለጫ

የኢፌዴሪ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ሚያዝያ 9 ቀን 2016 ዓ.ም በሚኒስትሮች ምክር ቤት መፅደቁን ተከትሎ - ፖሊሲውን ወደ ትግበራ ምዕራፍ ለማሸጋገር የሚረዱ የቅድመ-ዝግጅት ስራዎች ሲከናወኑ ቆይተዋል። ከነዚህ ስራዎች መካከል አንዱ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲውን አፈፃፀም፣ ክትትልና ድጋፍ ሥርዓት የሚመራ ፍኖተ ካርታ ማዘጋጀት ሲሆን - አሁን ላይ የፍኖተ ካርታው ዝግጅት ተጠናቆ ወደ ስራ እንዲገባ ተደርጓል።

በሌላ በኩል የሽግግር ፍትህ ፖሊሲው ካስቀመጣቸው ጉዳዮች አንዱ የሽግግር ፍትህ ስልቶችን የሚተገብሩ ነጻ እና ገለልተኛ ተቋማት ለማቋቋምና ለማደራጀት የሚያስፈልጉ የተለያዩ የሕግ ማዕቀፎች ዝግጅትን የሚመለከት ነው።

በዚህ መሰረት የአለም-አቀፍ ወንጀሎችን የሚደነግግ አዋጅ፣ የእውነት፣ ምህረት እና ማካካሻ ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ፣ እና የሌሎች የሽግግር ፍትህ አላባዎች ፈፃሚ ተቋማት ማቋቋሚያ አዋጆችን የማርቀቅ ስራ እየተሳለጠ ነው። በተጨማሪም በሽግግር ፍትህ ማእቀፍ የወንጀል ጉዳዮችን የሚያየው ልዩ ችሎት ስልጣንና አሰራርን የሚመሰርተው የሽግግር ፍትህ ልዩ ችሎት አዋጅ ዝግጅት በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አስተባባሪነት የሚከናወን ይሆናል።

የሕግ ማዕቀፎቹ ዝግጅት በጉዳዩ ላይ በቂ እውቀትና ልምድ ባላቸው ባለሙያዎች የሚካሄድ ሲሆን - አጠቃላይ ሂደቱ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ የሚጠናቀቅ ይሆናል። የህግ ማርቀቅ ስራው እንደተገባደደ ህዝቡና ባለድርሻ አካላት ዝርዝር አስተያየት የሚሰጡባቸው አገር-አቀፍ እና ዓለማቀፍ መድረኮች የሚዘጋጁ ይሆናል።

የነዚህ ሕጎች በፍጥነት መውጣት በፖሊሲው ላይ የተመላከቱትን ዓላማዎች ለማሳካት - በተለይም የተለያዩ የሽግግር ፍትህ ስልቶችን በመጠቀም እውነት ለማውጣት፣ እርቅ የሚወርድበትን አሰራር ለመመስረት፣ የወንጀል ተጠያቂነትን ለማስፈን፣ በቅድመ-ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ምህረትን ተግባራዊ ለማድረግ፣ የማካካሻና ተቋማዊ ማሻሻያ ስራዎችን ለማከናወን እና በአጠቃላይም የተሟላ ፍትህ ለማስፈን ቁልፍ ሚና ይጫወታል።

**የሽግግር ፍትህ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት**

**አዲስ አበባ**